


# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ ወታደራዊ መግለጫ

ጥቅምት 19 ቀን 2001 (ኦክቶበር 28 ቀን 2008)

## ከግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ ም. የተደረጉ ወታደራዊ ድሎች

1. ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም በአርማጭሆ ልዩ ቦታዉ ሆልመር በተደረገ የዉጊያ ዉሎ 50 የወያ ወታደሮች በመግደል፤ 30 በማቁሰል፤ 2 ብሬን መትረየስ፤3 እስናይፐር፤ 2 የመገነኛ ራዲዮኖችን፤30 ክላሽንኮፐ ለግንባሩ ገቢ ያደረገ ሲሆን፤አራት ምርኮኞችንም ማርኗል:: ከተማራኪቹ ዉስጥ የመቶ አለቃ ፈንቅል ይገኝበታል::

2. ግንቦት 28 ቀን በተደረገዉ የዉጊያ ዉሎ በሻምበል ቻሌ ዓለሙ የሚመራዉ የመከላከያ ልዩ ሃይልና ሚሊሺያ ቅልቅል በመደምሰስ፤ ሻምበሉን ጨምሮ 18 የወያኔ ወታደሮች በመግደል ሌሎች 10 ወታደሮችን አቁስሏል:: ሙሉ ትጥቃቸዉም ለግንባሩ ገቢ ሆኗል::

3. ሰኔ 17 ቀን በወልቃይት ልዩ ስሙ ማይሰገን በተባለ ቦታ 30 የወያኔ ወታደሮችን በመግደል 2 አቁስሏል:: እንደሲሁም 2 አስፓይነሮች፤3 በሬኖችንና ሙሉ ትጥቃቸዉን ለግንባሩ ገቢ አድርጓል::

4. ሰኔ 28 ቀን በአየር ማረፊያ ግጨዉ በተባለ ቦታ በተደረገዉ የዉጊያ ዉሎ 60 የጠላት ወታደሮችን በመግደል 30 በማቁሰል ሙሉ ትጥቃቸዉ ለግንባሩ ገቢ ሆኗል::

5. ሐምሌ 6 ቀን በአርማጭሆ ልዩ ቦታ አዋሳ ከወያኔ ልዩ የመከላከያ ሃይል ጋር በተደረገ የዉጊያ ዉሉ 15 ሲገደሉ 10 ቆስለዋል::

6. ነሐሴ 16 ቀን በጋብላ ልዩ ቦታዉ ለምለም ዉሃ የወያኔ ወታደሮች ነዋሪዉን ለአርበኞች የተለያ እገዛና ሽፋን ትስጣላችሁ በሚል የተሳሳተ መረጃ ሰላማዊ ዜጎችን ከማንገላታቱና ከማስቃየቱም አልፎ ችካኔ በተሞላበት ሁኔታ አቶ አዛነዉ ዋሴ የተባሉ አርሶ አደር በጥይት ደብድበዉ ሲገድሉ፤ ሁለት ሴቶችንና አንድ ህጻንን አቁስለዋል::

7. ጳ ጉሜ 1 ቀን ግጨዉ በተባለ ቦታ ከወያኔ ልዩ ሃይል ጋር በተደረገ ዉጊያ ዉሎ 10 የወያኔ ወታደር በመግደል፤ 5 በማቁሰል ሙሉ ትጥቃቸዉ ለግንባሩ ገቢ ሆኗል::

8. መስከረም 6 ቀን አዋሳ ልዩ ስሙ ዋት በተባለ የገጠር መንደር የወያኔ ልዩ ሃይል ጋር በተደረገ ዉጊያ 14 የወያኔ ወታደሮች ሲገደሉ 5 ቆስለዋል:: ሙሉ ትጥቃቸዉ ለግንባሩ ገቢ ሆኗል::

በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ኢትዮጵያኖች ግንባሩን እየተቀላቀሉ መሆናቸዉን ስንገልጽ፤ ድርጅታችን ሕዝባዊ መሰረቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እየደረሰና ከጎናችን እየተሰለፈ መሆኑን ማሳወቅ እንወዳለን::

**አንድነት ሃይል ነዉ!!!.**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ወታደራዊ መምሪያ ክፍል!!**